## ወይዘሪት ብርቱኳን ሚዴክሳ የአንድነት ፓርቲ ሊቀ መንበር መታሰርን አስመልክቶ ከዓለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ሕብረት ለፍትሕና ዲሞክራሲ የተሰጠ መግለጫ።

## Tigrean International Solidarity for Justice and Democracy

በአንድ ሀገር የሕግና የፍትሕ ዋስትና ከሌለ የዜጎች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ይከበራሉ ብሎ ማሰብ አይቻልም። የህዝብና የሀገር ድሕንነት በአግባቡ ካልተጠበቁ ደግሞ ልማት፣ ሰላም፣ ዲሞክራሲና ዕድገት ሊመጣ ይችላል ብሎ ለማመንም ያስቸግራል። በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ በየማዕዝናቱ በተለይም በአፍሪቃ አህጉር በበርካታ ሀገሮች እየተከሰቱ ያሉት ፓለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ቀውሶችም መነሻቸው የፍትሕ አልባነትና የአፈና ውጤቶች መሆናቸው እሙን ነው።

በሀገራችንም ኢሕአዴግ ስልጣን ላይ ሲወጣ ካለፈው ታሪክ ተምሮ ህዝቡ የስልጣን ባለቤት የሚሆንበት ሁኔታ በማመቻቸት አዲስ ምዕራፍ ይከፍት ይሆናል ተብሎ የተሰፋ ጭላንጭል ተጥለበት እንደነበር አይዘነጋም፡፡ ሆኖም በ18 ዓመታት የስልጣን ዘመኑ በሂደት ያሳየው ባህርይና ለኢትዮጵያ ህዝብ ያስገኘው ድምር ውጤት ስንመለከት ግን በወሳኝ መልኩ የነበረው ተስፋ እየጨለመ ነው፡፡ ይባስ ብሎ ለዘመናት ያካበትናቸውን ታሪካችንና አንድነታችን የሚንድ፤ የዜጎች ሰብአዊ ዲሞክራሲያዊ መብቶችንና የህዝቡ የተሳትፎ አድማስ የሚያጠብ፤ በአጠቃላይ የሀገራችን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል ስራ በመስራት ራሱ የገነባውን ራሱ መልሶ ሲያፈርስ ታይቷል፡፡

ሰሞኑን የአንድነት ፓርቲ ሊቀ መንበር በሆኑት በወይዘሪት ብርቱኳን ሚዴክሳ ላይ ሕግና ስርዓት ባልተከተለ መልኩ የታሰሩበት አሳዛኝ ሁኔታ ስንመለከትም ከላይ እንደተጠቀሰው በሀገራችን ያለው ምስቅልቅል የፓለቲካ ባህርይ የፈጠረው ዉጤት ነው፡፡ ኢሕአዴግ በአንድ በኩል ሕገ መንግስት መከበር አለበት ብሎ ሲናገር ይታያል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ህዝቡ ሕገ መንግስቱ የሰጠውን መብት ተጠቃሚ እንዳይሆን መሰናክል በመፍጠር ሕጉን ራሱ ሲያፈርስና ሕገ ወጥ ስራ ሲሰራ ይገኛል፡፡ ኢሕአዴግ በአንድ በኩል በሕጋዊና ሰላማዊ ትግል ተወዳድሮ በህዝብ ዳኝነት ስልጣን የመያዝ አስፈላጊነት ይናገራል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የውድድር መድረኩን የሚያጠብ፣ ሰላሙን የሚያደፈርስና የዜጎች የለውጥ ተስፋን አጨልሞ የአንድ ፓርቲ ዘላለማዊነት የሚያረጋግጥ ስራ እየሰራ ይገኛል፡፡ ታዲያ! ይህን ዓይነት እርስ በርሱ የሚቃረን ፓሊሲ እያራመዱ በሀገሪቱ ዘላቂ ዲሞክራሲ፤ ልማትና ዕድገት መገንባት ይቻላልን? ይህ ዓይነቱ ተግባር ከተደጋገመስ ዉሎ አድሮ ወዴት ያመራል?

ወይዘሪት ብርቱኳን ሚዴክሳ እንደሚሉት "እኔ የአላማና የአመለካከት ልዩነት እንጂ የሰው ጠላት የለኝም፡፡ ኢሕአዴግን የምቃወመው በሚያራምደው ፓሊሲ እንጂ እንደጠላትና ባዕድ በማየት አይደለም። ኢሕአዴግም እንደማንኛወም ድርጅት ታግሎና ተወዳድሮ ስልጣን ለመያዝ መብት ያለው ኢትዮጵያዊ ድርጅት መሆኑን አምናለሁ፡፡ እኔ የምታገለው አንድ ዲክታተራዊ ስርዓት አስወግዶ በሌላ ዲክታተራዊ ስርዓት ለመተካት ሳይሆን ኢሕአዴግን ጨምሮ ለሁላችን የሚሆን የስርዓት ለውጥ ለማምጣት ነው፡፡ በጉልበት የሚመጣ መንግስት ዘላቂነትና ዋስትና እንደሌለው ሁሉ በታሪካችን ያየነውና አሁንም የምናየው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም ያለውን ቀዳዳ ተጠቅሞ ሰላማዊ ትግል ማካሄድ የበለጠ አማራጭ ነው ብየ እምናለሁ፡፡ ሰላማዊ ትግል ማካሄድ አለብን ስንልም መንገዱ ሁሉ አልጋ ባአልጋ እንዳልሆነ እሙን ነው፡፡ መስዋእትነት ይጠይቃል፡፡ መታሰር፣ መንገላታትና ማስፈራራት እንዳለው አምነን በመቀበል በሀገራችን ለውጥ ማምጣት ይቻላል" የሚል ነው፡፡ ይህ ማለትም ለሕግ የበላይነት፣ ለሰላማዊ ትግል፣ ለዜጎች እኩልነትና አንድነት ያላቸውን የኣላማ ፅናትና የለውጥ ቁርጠኝነት የሚያመለክት ነው፡፡

ወይዘሪት ብርቱኳን ሚዴክሳ ከዚህ ፅኑ አስተሳሰባቸው በመነሳት ብዙዎቹ የኢትዮጵያ ፓለቲከኞች በሀገራችን ውስጥ ያለው ተጨባጭ እውነታ ማየትና ማመን አቅቷቸው ታጥቦ ጭቃ ሆነው የቀሩበት፣ ፈታኝ የትግል መድረክ በመጣ ቁጥር ዳገት መውጣት አቅቷቸው ተበታትነው የቀሩበት፤ ህዝብና መንግስት ለይተው መታገልና ማታገል አቅቷቸው እንዲሁ በጀምላ የጥላቻ ፓለቲካ አንግበው ቂም በቀል የሚያስተምሩበት፤ ከሀገር ጥቅምና ድህንነት በላይ የራሳቸውን የግል ጥቅም በማስቀድም ለፍቅረ ንዋይና ለስልጣን ሲሉ የተምበረከኩበት፤ በአጠቃላይ ብዙዎቹ በኋላ ቀር የፓለቲካ ባህልና በጠባብ የትግል ቀለበት ውስጥ ገብተው ሊወጡበት ያልቻሉትን የአዙሪት ሰንሰለትና አጥር ሰብረው በመውጣት በኢትዮጵያ ውስጥ የህዝቡን ልብ ትርታ የሚነካ አዲስ የአመለካከት እመርታና አዲስ የትግል ምዕራፍ ሊከፍት የሚችል መድረክ ፈጥሯል፡፡

ይህ ሁሉ መነሻ አድርገን ስናይ ከሁሉ በላይ የወይዘሪት ብርትኳን ሚዴክሳ ትልቁ ቁም ነገር ከቃሊቲ እስር ቤት ሲወጡ በገቡበት ቃል መሰረት የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት ተቀብለው፣ አመፅን በመቃወም ሰላማዊ የትግል መርሕ መርጠው፣ የኢሕአዴግ መንግስት ያወጣውን ሕግና ስርዓት አክብረው፤ ሕጋዊ ፍቃድ ያለው የፓለቲካ ድርጅት አቋቁመው፣ በሀገራቸውና በአላማቸው ተማምነው በህዝባቸው መሃል የሚኖሩና የሚታገሉ ሰላማዊት ዜጋ መሆናቸውን ነው። ስለሆነም እንደ ብርትኳን የመሰሉ የሰለጠነ፣ ሰላማዊ አመለካከትና የፓለቲካ ብስለት ያላቸው ሰዎች ለዲሞክራሲ ግንባታና ለሕግ የበላይነት ማረጋገጥ ሲባል እንደ ጥሩ ተምሳሌት ተወስደው መከበር፣ ማበረታታትና መደገፍ ያለባቸው ናቸው እንጂ <u>አፍ እላፊ</u> ተብሎ በትንሽ ነገር ለእስራት መዳረግ፣ ማስፈራራት፣ መንገላታትና መኮርኮም የሚገባቸው አይደሉም፡፡

እኛ ዓለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ሕብረት ለፍትሕና ዲሞክራሲ የወይዘሪት ብርቱኳን ሚዴክሳ ጉዳይ ያሳዘነንና ያስቆጣን እስር ቤት መግባታቸው አዲስ ስለሆነብን ወይም ከሳቸውም ሆነ ከሚመሩት ፓርቲያቸው ጋር ልዩ የፓለቲካ ትስስር ስላለንም አይደለም፡፡ በዚሁ ጉዳይ ላይ ተቃውሞዋችንን እንድናሰማ ያነሳሳን ትልቁ ጉዳይ በያንዳንዱ ዜጋ ላይ የሚደርሰውን የሰብአዊ መብት ረገጣና ጥሰት ጥብቅና መቆም ወገናዊና ሞራላዊ ግዴታ ስላለብን ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ፡

1. መንግስት የዜጎቹን ድሕንነት ለመጠበቅ ሕግና ስርዓት ማስከበር ሐላፊነት እንዳለው እናምናለን፡፡ ነገር ግን ሕግና ስርዓት ማስከበር የሚቻለው ከሁሉም በላይ ሕግና ስርዓት የሚገዛው መንግስት ሲኖር ብቻ ነው፡፡ መንግስት ራሱ ያወጣቸውን ሕጎችና ደንቦች ሲያከብር ነው። ለራሱ ከሕግ በላይ ሆኖ ስለሕግ ማስተማርና ስለዜጎች ድሕንነት መጠበቅ የሚባል ነገር ፈፅሞ የማይቻል ነገር ነዉ፡፡ በወይዘሪት ብርቱኳን ላይ የቀረበው ክስና የአፈፃፀሙ ሁኔታ ስንመለከትም ጉዳዩ ሕጋዊ መሰረት የሌለው፣ በቃላት ጨዋታና በጠጉር ስንጠቃ ላይ የተመሰረተ፣ ለፓለቲካ ጠቀሜታ ተብሎ የተወሰደ የፕሮፓጋንዳ ጥቃት መሆኑን በሚገባ ተገንዝበነዋል፡፡

2. ምርጫ በተቃረበ ቁጥር በተቃዋሚ ድርጅቶችና በመሪዎቻቸው የሚደረገው ወከባ፣ መሰናከልና የስነ ልቦና ጥቃት የተለመደ ተግባር እየሆነ ሄዷል፡፡ ይህ እርምጃም በሕገ መንግስቱ የሰፈሩ የዜጎች መብቶችና መርሆችን ከመጣረሩም በላይ በሀገራችን ውስጥ ነፃ የውድድር መድረክ እንዳይፈጠር፤ ኢሕአዴግን የሚፎካከሩ ብቃት ያላቸው የፓለቲካ ድርጅቶችና መሪዎች በሀገሪቱ እንዳይበቅሉ፤ ህዝቡ ለለውጥና ለዲሞክራሲ ያለውን ተስፋ እንዲጨልም፤ ዜጎች ከሰላማዊ የትግል መድረክ አግልሎ ወደ አመፅ የሚገፋፉ ስራ ነው ብለን እናምናለን፡፡ ስለሆነም ኢሕአዴግ ራሱ መንግስት ራሱ ተወዳዳሪ ፓርቲ ሆኖ ከግለ ሰዎችና ከግለ ድርጅቶች እልህ ገብቶ ከመናቆርና ተስፋ አስቆራጭ የሆኑ ተግባራት ከመፈፀም ይልቅ ሆደ ሰፊ ሆኖ በትላልቅ ጉዳዮች ላይ በማትኮር ለዲሞክራሲና ለልማት ግንባታ የሚያመች ስራ ቢሰራ ለህዝብም ለሀገርም ለራሱ ለኢሕአዴግም ይበጃል ብለን እናምናለን፡፡

3. <u>*ለውጥ የጠማውና በልቡ የሸፈተ ህዝብ በማሰርና በማስፈራራት ማንበርከክ እንደማይቻል*</u> ከመፅሐፈ ታሪክ ብቻ ሳይሆን ኢሕአዴግ ራሱ የመጣበት ሂደት ነው፡፡ የአንድ ታጋይ መታሰር ሽሕ ታጋዮችን ያፈራልና ነው፡፡ የወይዘሪት ብርቱኳን ሚዴክሳ ያለ አግባብ መታሰርም ሁኔታውን ያባብሰዋል እንጂ አያረግበውም፡፡ ህዝቡን የበለጠ ያስተባብረዋል እንጂ አይበትነውም፡፡ ትግሉም የበለጠ ያፋፍሟል እንጂ አያዳፍነውም፡፡ ስለዚ መንግስት የጉዳዩን አሳሳቢነትና የህዝቡን ጭኾት ተገንዝቦ በወይዘሪት ብርቱኳን ሚዴክሳ ላይ የበየነውን እስር እንዲሽር እንጠይቃለን፡፡

ዓለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ሕብረት ለፍትሕና ዲሞክራሲ
ጃንዋሪ 13 ቀን 2009 ዓ/ም
ሰሜን አሜሪካ